# ያልተዘገቡ የምርጫ 2002 ሕገወጥ ድርጊቶች በአንዳንድ የደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች

**(ጥንቅር አንድ)** ግንቦት 17 2002 ዓ.ም.

*ይህ የመረጃ ጥንቅር የተዘጋጀው ቀድሞም በነበረው አሁን ግን ይበልጥ አደገኛና አስፈሪ በሆነው መንግሥታዊ እመቃ ሥር ነው:: አዘጋጆቹ በራስ ተነሳሽነት የተንቀሳቀሱ ቁጥራቸውም ሆነ አቅማቸው ውሱን የሆነ እና የየትኛውም የፖሊካ ፓርቲ አባል ያልሆኑ ገለልተኛ ነገር ግን ነጻነትና ሐገር ወዳድ ዜጎች ናቸው:: ይህ የተባለው (ግልጹን ነገር ለመድገም) አንድም መረጃው የተሰበሰበበትን አስጨናቂና የማይመች የፖለቲካ ድባብ ለማሳየት ነው:: በተጨማሪ በአንድ ፊት ስለ ጥንቅሩ ውሱንነትና በሌላ በኩል ግን ስለተአማኒነቱ መጠንም የሚጠቁመው ነገር ካለ በሚል ነው:: ጥንቅሩ ደረጃውን እንደጠበቀ የተሟላ ምርመራና ዘገባ ተደርጎ ሊቆጠር አይገባም ለማለትም ነው:: ይልቁንም ጥንቅሩ ሰፋ ላሉ የምርመራና የማጣራት ሥራዎች በመነሻነት የሚያገለግሉ ጥቆማና መረጃዎችን ነው በዋነኝነት የያዘው::*

## መግቢያ

የ2002 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ምርጫ፤ ገዢው ፓርቲ/መንግሥት ለ5 ዓመት ያህል በተዘጋጀበት መሠረትና በሁሉም ዘንድ እንደተጠበቀው፤ በግልጽም በሥውርም በተካሄደ ከፍተኛ ማጭበርበር የገዢው ፓርቲ/መንግሥት "አሸናፊነት" ተረጋግጦ ተፈጽሞአል:: ገዢው ፓርቲ ከምርጫው በጣም ቀደም ብሎም ሆነ በድምጽ መስጫው ቀን የዋዜማ ምሽትና ሌሊት፤ እንዲሁም በድምጽ አሰጣጡ ሂደትና በቆጠራው ወቅት በግልጽና በስውር ስለፈጸማቸው የማጭበርበር ድርጊቶች ተጨባጭና ዝርዝር መረጃዎችና ማስረጃዎች ወደፊት በቅርቡ ከልዩ ልዩ አቅጣጫዎች በተከታታይ እንደሚጎርፉ (አዎ እንደሚጎርፉ) ይታመናል::

ከሌሎች የሐገራችን ክልሎች ጋር ሲነጻጸር፤ ከምርጫው ጋር በተያያዘ በደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝብና በክልሉ በየደረጃው በሚንቀሳቀሱ ልዩ ልዩ ተቃዋሚ ኃይሎችና ደጋፊዎቻቸው ላይ ከምርጫው በፊትም ሆነ አሁን እየደረሰ ያለው ሕገ ወጥ ድርጊት በተመጣጣኝ ሁኔታ ተመዝግቦ ተዘግቦአል ለማለት አያስደፍርም:: በውል ከምናውቃቸው አንዳንድ ተጨባጭ (ውጫዊና ውስጣዊ) ችግሮችም የተነሣ ይህ ስለደቡብ ኢትዮጵያ የሚታየው ምርጫ-ነክ የመረጃ ክፍተት ቀጣይነት እንዳይኖረው ያሰጋል:: ይህ እንዳይሆን የሚመለከታቸው ዜጎች ሁሉ የሚችሉትን ዓይነትና ያህል አስተዋጽዖ በማድረግ የግል-የዜግነት ኃላፊነታቸውን እና ሐገራዊ ግዴታቸውን ይወጡ ዘንድ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ እናደርጋለን::

## የጥንቅሩ ዓላማ፤ የመረጃ ምንጮችና መረጃ የተሰበሰበባቸው መንገዶች

የዚህ አነስተኛ ጥንቅርና ምናልባትም የቀጣዮቹም ዓላማ በምርጫ 2002 ዙሪያ ስለ ደቡብ ኢትዮጵያ ሊታይ የሚችለውን የመረጃና የማስረጃ ክፍተት ለማጥበብ በመሞከር ሐገር አቀፋዊው የምርጫ ሥዕልና መረጃ (አስከፊና አሳዛኝ ቢሆንም) ይበልጥ የተሟላ እንዲሆን ማገዝ ነው:: የጥንቅሩ ዓይነተኛ ዓላማ፤ የሚመለከተው ወገን ሁሉ መረጃዎቹን መነሻ በማድረግ ከዋናዎቹ ምንጮች በይበልጥ አጣርቶና አረጋግጦ ይፋ እንዲያደርግና በመረጃ ለተደገፈ የማስተካከያ ውሣኔ የበኩሉን አስተዋጽዖ እንዲያበረክት የመነሻ ጥቆማዎችን መስጠት ነው::

- አንዳንዶቹ ክስተቶች፤ የጽሁፍ መረጃዎችና ለምሳሌ የተሰረቁ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ቅጂዎቹን ሣይሆን ዋናዋቹን ማስረጃዎች የጥንቅሩ አዘጋጆች በዓይናቸው አይተው ያረጋገጧቸው ናቸው፤
- ለሚበዙት መረጃዎች የመነሻ ጥቆማዎች የተገኙት በልዩ ልዩ የደቡብ ኢትዮጵያ አከባቢዎች (ሞያሌ፤ ቦረና፤ ሐገረ ማርያም፤ ይርጋ ጨፌ፤ ዲላ፤ አለታ ወንዶ፤ አርባ ምንጭ፤ ኮንሶ፤ ወንዶ ገነት፤ ጥቁር ውኃ እና የሀዋሳ አጎራባች ወረዳዎች ውስጥ ኗሪ ከሆኑ ገለልተኛ ዜጎች ነው፤
- ከገለልተኛ ዜጎች የተገኙትን መረጃዎች ከምንጫቸው ለማጣራት፤ ለማመሳከርና ለማረጋገጥ አቅም የፈቀደውን ያህል ሙከራ ተደርጓል:: ለዚህም የሚመለከታቸውን የተቃዋሚ ድርጅቶች (መኢአድ፤ መድረክ፤ ሲአን) የአካባቢ አመራሮች፤ አባላት፤ ደጋፊዎችና የምርጫ

ተወካዮች/ታዛቢዎች በግንባርና በስልክ በማግኘት በጽሁፍና በቃል የሰጡትን መረጃና ማረጋገጫ ለማካተት ጥረት ተደርጓል፤

- መረጃዎቹ ከመላው ደቡብ ኢትዮጵያ የተሰበሰቡ አይደሉም፤ ሆኖም ከክልሉ ዋና ከተማ (ሀዋሳ) እስከ አርባ ምንጭና ኮንሦ እንዲሁም እስከ ሞያሌ የሚገኙ የአንዳንድ አካባቢዎችን የምርጫ ሁኔታና አፈጻጸም እንደሚሸፍኑ ከቀረበው ጥንቅር መረዳት ይቻላል::

## <u>የእመቃ፤ የፍርሐት፤ የሥጋትና የጥርጣሬ ድባብ መስፈን</u>

"ምርጫ" 2002ን በሚመለከት የመረጃ ክፍተት እንዲኖር ያደረጉ/የሚያደርጉ በርካታ የተለያዩ ምክንያቶች ተስተውለዋል:: ወቅታዊው ምክንያት የጊዜው አጭርነት ነበር:: የተቃዋሚ ድርጅቶች የየአካባቢው መዋቅሮች ቀልጣፋ ያልሆነ አሠራርና ያልተጠናከሩ መዋቅራዊ ግንኙነቶችም ለመረጃ ፍሰት መሰናክል ሲሆኑ እየታየ ነው:: ከሁሉም የሚብሰው፤ እጅግ የሚያሳስበውና የሚያሰጋው እንቅፋት ግን በ"ምርጫ"ው ማግሥትም እየተባባሰ የመጣው የፍርሐትና የሥጋት ችግር ነው:: ይህ ሰፊና አስፈሪ አንደምታ ያለው ችግር ነው::

የሕዝቡን ሌላ ሌላ ስሜት ለጊዜው እንለፈው:: የተቃዋሚ ድርጅቶች የደቡብ አካባቢ መዋቅሮች <u>አንዳንድ</u> አመራሮችና ዕጩ ተወዳዳሪዎች፤ በርካታ አባሎች፤ ደጋፊዎቻቸውና የምርጫ ታዛቢዎቻቸው በተስፋ መቁረጥ፤ የፍርሐትና የሥጋት ስሜት እንደተዋጡ ይታያል:: ሲዛትባቸው እንደነበረው ሁሉ ሲፈሩትና ሲጠብቁት የነበረው "የአሸናፊዎች" መንግሥታዊ የበቀል ጥቃት የሚፈጸምበት ጊዜ አሁን ስለመሆኑ እየገለጹ ነው:: አንዳንዶች ከአሁኑ አንዳንድ ምልክቶች ማየት መጀመራቸውን ይገልጻሉ:: ከዛሬ ነገ እንታሠር ይሆናል በሚልና በመሳሰለው የፍርሐትና የሥጋት መንፈስ ውስጥ ገብተዋል:: የነዚህ ወገኖች ሥጋት መሠረተ-ቢስ ነው ሊባል አይችልም፤ አይገባምም:: ለተቃዋሚዎች ሲሰጥ የቆየውን "ከምርጫ በኋላ እንከሳችኋለን - እናስራችኋለን" የሚለውን ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ በግልጽ ያውም በፓርላማና በመገናኛ ብዙኃን ሳይቀር የሰማነው ነው:: በከተማና በገጠር የቀበሌ አመራሮችና ካድሬዎች በተቃዋሚ አመራሮች፤ በዕጩ ተወዳዳሪዎች፤ በምርጫ ታዛቢዎቻቸው፤ በአባላትና በደጋፊዎቻቸው ላይ በግለሰብ ደረጃ የፈጸሙባቸው ዛቻና ማስፈራሪያም የመንግሥታዊው ማስጠንቀቂያ አካል ነበር:: አሁን የሚታየውን የአንዳንድ ተቃዋሚዎችንና ደጋፊዎቻቸውን የፍርሃትና የሥጋት ስሜት በቅጡ መረዳት የምንችለውና የሚገባንም ከዚህ በመነሣት ነው:: አሁን እየታየ ያለው ምላሻቸውም ራስን በማዳን ላይ ያተኮረ ነው:: ስለምርጫው ጉድለቶች በተጨባጭ ያዩትንና የሰሙትን ከመመስከርና መረጃ ከመስጠት የመቆጠብ - በራስ ላይ ማዕቀብ የመጣል - እንዲሁም ራስን ከእንቅስቃሴ የማግለል አዝማሚያዎች እየታዩ ነው::

ምናልባት እንደሌላው የሐገሪቱ አካባቢ ሁሉ፤ ይህን መሰል የእመቃ፤ የፍርሐት፤ የሥጋትና የጥርጣሬ ድባብ በደቡብ ኢትዮጵያም ሰፍኖ መቆየቱን ማወቁና ማሳወቁም በራሱ አንድ መረጃ ነው:: በዚህ ድባብ ውስጥ በመሥራት ለጊዜው የተገኙት ዋና ዋና መረጃዎች በሁለት ክፍል ተከፍለው እንደሚከተለው ቀርበዋል::

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ቅድመ ምርጫ 2002</u>

በተለያዩ የደቡብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ነዋሪ ከሆኑ ዜጎች ከተገኙ የቅድመ ምርጫ 2002 (ከመራጮች ምዝገባ ጀምሮ) መረጃዎች መካከል በተደጋጋሚ የሚጠቀሱት ስሞታዎች የሚከተሉት ናቸው:

### ሀ) <u>ማታለል፤ ማስፈራራት፤ ማዋከብ፤ ዛቻና ድብደባ</u>

- በተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች ላይ (ቤተሰቦቻቸውና ዘመዶቻቸውን ጨምሮ) ከምርጫው ጋር በተያያዘ ተደጋጋሚ ማስፈራራት፤ ዛቻና ድብደባ ይፈጸም ነበር፤
- በአንዳንድ የገጠር አካባቢዎች ዜጎች የተቃዋሚ ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎች በመሆናቸው ብቻ ከሴፍቲ ኔት (የምግብ ለሥራ) ፕሮግራም ይባረሩና የምግብ እርዳታም ይነፈጉ ነበር፤

- ኢሕአዴግን ካልመረጣችሁ ሴፍቲ ኔትና እርዳታ አታገኙም፤ ኢሕአዴግን ከመረጣችሁ ግን ለሚቀጥለው 5 ዓመት የሴፍቲ ኔትፕሮግራምና እርዳታ ተጠቃሚ ትሆናላችሁ የሚል ማስፈራሪያና ማባበያ የተለመደ ከስተት ሆኖ ነበር፤
- ብዙ ሰዎች የተቃዋሚ ፓርቲ አባልነታቸውን እና ደጋፊነታቸውን ትተው የገዥው ፓርቲ አባል እንዲሆኑ ከማባበያም ባለፈ ዛቻና ማስፈራሪያ ደርሶባቸዋል፤
- የእርዳታና ሴፍቲ ኔት ተጠቃሚ የሆኑ ዜጎችን ስም ከቀበሌ መዝገብ በመውሰድ፤ የመራጮች ካርድ በስማቸው በማዘጋጀት በአካባቢ ታጣቃዎች አማካኝነት በየቤቱ እየተዞረ እንደታደለ፤ (አንድ ታጣቂ ለ70 እና 80 ሰው እንዲያድል ተደርጓል)::
- በአንዳንድ አካባቢዎች የተቃዋሚዎች አባላትና ደጋፊዎች የመራጮች ካርድ እንዳይወስዱ ተከልክለዋል፤
- በአንዳንድ አካባቢዎች ኢሕአዴግን ካልመረጣችሁ በኢሕአዴግ ያገኛችሁት የኃይማኖት ነጻነታችሁ ይገፈፋል፤ ተቃዋሚዎችን ከመረጣችሁ እንደ ደርግ ጊዜ በኃይማኖታችሁ ላይ ከፍተኛ ችግርና አደጋ ይደርስባችኋል የሚል የማስፈራሪያ ቅስቀሳ ተደርጓል፤
- የየአካባቢው የመንግሥትና የገዢው ፓርቲ ኃላፊዎችና ካድሬዎች፤ ህዝቡን እየሰበሰቡ የምትመርጡት ማንን ነው? ኢሕአዴግን የሚቃወም አለ ወይ? ከሚሉ ማስፈራሪያዎች ጀምሮ፤ ኢሕአዴግን ለመምረጣችሁ ከወዲሁ ፈርሙ፤ ካልፈረማችሁ ከሴፍቲ ኔት ፕሮግራም ትሠረዛላችሁ፤ ዕርዳታ አታገኙም፤ በማለት ህዝቡ ፈርቶ እንዲፈርም አድርገዋል፤ በተጨማሪም አሁን እዚህ ፈርመህ በምርጫው ወቅት ግን ተቃዋሚ መርጠህ ብትገኝ ፊርማህ ተመርምሮ እርምጃ ይወሰድብሀል በሚል በህዝብ ላይ ፍርሐትና ስጋት እንዲፈጠር ተደርጓል፤

## ለ) <u>የምርጫ አስፈጻሚዎችና የሕዝብ ታዛቢዎች</u>

እንደ ሌላው የኢትዮጵያ አካባቢ ሁሉ በደቡብ ኢትዮጵያም አብዛኞቹ የምርጫ አስፈጻሚዎችና የሕዝብ ታዛቢዎች የገዥው ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ናቸው:: ለዚህ ስሞታ ተጨባጭ ማረጋገጫ ይሆናሉ በሚል አንዳንድ ምንጮች የሚከተሉትን መረጃዎች በማስረጃነት አቅርበዋል:

### 1) <u>በምርጫ ኃላፊነት/አስፈጻሚነት/አስተባባሪነት በምርጫ ቦርድ የተመደቡ</u>

1.1) <u>የቦረና ዞን</u> የምርጫ አስተባባሪ አቶ በቀለ ኢላላ የኦህዴድ/ኢሕአዴግ አባል ነው፤ ሌሎቹም የዞኑ የወረዳና ቀበሌ ምርጫ አስፈጻሚዎች የገዥው ፓርቲ አባላት ናቸው፤

1.2) <u>የቦርቻ ወረዳ</u> (ሲዳማ ዞን) የምርጫ ቦርድ ኃላፊ የሆነው አቶ ደጀኔ አሰፋ፤ የደኢህዴን/ኢሕአዴግ አባል፤ የቦርቻ ወረዳ አስተዳደር የዶኩሜንቴሽንና የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ከፍተኛ ኦፊሰር ነው፤::

1.3) <u>በይርባ</u> (ሲዳማ ዞን) ምርጫ ክልል ምርጫ አስፈጻሚ የሆነው አቶ ኤልያስ የኢሕአዴግ የወጣት ሊግ አባል ነው፤ ከቦርቻ ወረዳ የደኢህዴንን ወጣቶች ወክሎ አዲስ አበባ ሄዶ ሐገር አቀፍ የኢሕአዴግ ወጣቶች ስብሰባ ላይ የተካፈለ የደኢህዴን አባል ነው::

1.4) <u>በፉላሳ ምርጫ ጣቢያ</u> (ሲዳማ ዞን) የተመደቡ ምርጫ አስፈጻሚዎች:

1) አቶ ማርቆስ ቀንጠሎ የፉላሳ ምርጫ ጣቢያ ኃላፊ የሆነው የቀበሌው ደኢህዴን መሠረታዊ ድርጅት ምክትል ሰብሳቢ ነው፤
2) አቶ ማርቆስ አብርሐም የምርጫ ጣቢያው አስፈጻሚ አባል የሆነው የቀበሌው ደኢህዴን መሠረታዊ ድርጅት ጸሀፊ ነው፤

### 2) <u>በህዝብ ታዛቢነት የተመረጡ</u>:

2.1) <u>በቦርቻ ወረዳ</u> በቦነያ ጭሪ ቀበሌ የተመረጡ:

1.1) አቶ ኡቴ ቤነና የቦርቻ ወረዳ ደኢህዴን አባል፤
1.2) አቶ ግርማ እሳቱ የቀበሌው (ቦነያ ጭሪ) ደኢህዴን መሠረታዊ ድርጅት ሰብሳቢ፤
1.3) አቶ ጃሣ ጀምቦላ የቀበሌው (ቦነያ ጭሪ) ደኢህዴን መሠረታዊ ድርጅት አባል፤
1.4) አቶ ኢዩኤል ሀሚሶ << << << << <<
1.5) ወ/ሮ ዘሪቱ ደሴ የቀበሌው የደኢህዴን ሴቶች ኃላፊ

**2.2)** <u>በፉላሳ ምርጫ ጣቢያ</u> የተመረጡ:

2.1) አቶ ኤርምያስ ፊሳ የቀበሌው ታጣቂና የደኢህዴን አባል
2.2) አቶ አያሞ አሬዶ የደኢህዴን አባል
2.3) አቶ ሲራጅ ደበሎ << <<
2.4) አቶ ሙሴ ቦኩላ << <<
2.5) አቶ ቦረሶ ባንገሳ << <<

እንደምንጮቹ ጥቆማ ከሆነ ከላይ የተዘረዘሩት የምርጫ አስፈጻሚዎችና የህዝብ ታዛቢዎች ለአብነት ያህል የተጠቀሱ ናቸው፤ ምንጮቹ፤ በሁሉም ሥፍራ የገዢው ፓርቲ መመሪያና አሠራር አንድ አይነት በመሆኑ የምርጫ አስፈጻሚዎች አመዳደብና የህዝብ ታዛቢዎች አመራረጥም ከዚህ የተለየ አልነበረም ነው የሚሉት::

## ክፍል ሁለት:

## የምርጫ ዋዜማ፤ የድምጽ አሰጣጥና ቆጠራ ሁኔታ

በሲዳማ ዞን 19 የምርጫ ክልሎች ይገኛሉ:: የሲአን ከፍተኛ አመራር በግንቦት 10 እና 17 / 2002 ዓ.ም. ለምርጫ ቦርድ በጻፋቸው ደብዳቤዎች ከምርጫው በፊትና በምርጫው ቀን ደረሱ ያላቸውን ሕገ ወጥ ድርጊቶችና ችግሮች ዘርዝሮ ምርጫው በአጠቃላይ "የተጭበረበረ ኢ-ዴሞክራሲያዊ በመሆኑ በሲዳማ ክልል በ19ኙም የምርጫ ክልሎች ምርጫው እንዲደገም ድርጅቱ አበክሮ" ጠይቋል:: ከዚህ በታች የቀረበው መረጃ የተገኘው ከመራጮች፤ ከገለልተኛ ወገኖች፤ ከሲአን አመራርና በየደረጃው ከሚንቀሳቀሱ የሲአንና የሌሎች ተቃዋሚዎች አባላትና ደጋፊዎች ነው::

### 1) <u>አለታ ወንዶ ምርጫ ክልል</u> (ሲዳማ ዞን)

1.1 በአለታ ወንዶ ምርጫ ክልል በነበሩት 14 የምርጫ ጣቢያዎች ከሞላ ጎደል ሁሉም የተቃዋሚዎች ተወካይ/ ታዛቢዎች በአፈናና በተደጋጋሚ ማስፈራሪያ የተነሳ <u>ቤታቸው እንዲቀሩ</u> ወይም <u>የሄዱት</u> <u>ወደ ድምጽ መስጫ ጣቢያ እንዳይገቡ</u> ወይም <u>ከገቡ በኋላ ለቀው እንዲወጡ በመገደዳቸው</u> ወይም <u>የሕገ ወጥ ድርጊት ተባባሪ ለመሆን ባለመፈለግ</u> የምርጫ ጣቢያዎችን ለቀው ለመሄድ ተገድደዋል:: በነዚህ ምክንያቶች ምርጫው የተቃዋሚዎች ተወካዮች /ታዛቢዎች በሌሉበት ተጀምሮ ተፈጽሟል:: (ቀበሌዎቹ ገርቢቾ ኪላ፤ ኪሌ ጨቅቻ፤ ሐወኛ፤ አጋራ ጌድሌ፤ ሜጫ፤ ዊቾ ቡሌ፤ መንትዮ፤ ሆንዶባ፤ ጊዲቦ፤ሕንሰሳና ኤርዳማ ወዘተ ናቸው):: <u>ለማሣያ ያህል</u>:

- ሀ) መንትዮ ቀበሌ 01-ሀ እና 01-ለ የተቃዋሚዎች ታዛቢዎች ከገዢው ፓርቲ ከድሬዎች ተደጋጋሚ ማስፈራሪያ ስለደረሳቸው በድምጽ መስጫው ቀን ሊገኙ አልቻሉም፤
- ለ) በገርብቾ ኬላ ቀበሌ 3 ምርጫ ጣቢያዎች (01-ሀ፤ 01-ለ እና 02-ሀ) የተቃዋሚ ታዛቢዎች ከገዢው ፓርቲ የደረሰባቸውን ጫና መቋቋም ስላቃታቸው የምርጫ ጣቢያውን ለቀው ለመሄድ ተገደዋል፤
- ሐ) በኬላ ሄጢቻ 3 ምርጫ ጣቢያዎች (01-ሀ፤ 01-ለ እና 02-ሀ) በድምጽ አሰጣጥና ቆጠራ ሂደት የነበረውን ሕገ ወጥ አሠራር በመቃወም የሁሉም (መድረክ፤ ሲአን፤ መኢአድ፤ ኢዴፓ) ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ወኪሎች በመተማመኛ ሠነድ ላይ አልፈረሙም::

1.2 በአለታ ወንዶና ጭኮ ወረዳዎች ለየአራት ቀበሌዎች አንድ ተዘዋዋሪ ችሎት በመመደብና ዳኞችን በቅርብ በማስቀመጥ የምርጫ ሕግ ጥሰዋል የሚሏቸው የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ላይ ፈጣን የፍርድ ውሳኔ ለመስጠት ተቀምጠው ነበር:: :

### 2) <u>ቦርቻ ወረዳ (ምርጫ ክልል)</u> ሲዳማ ዞን

በቦርቻ ወረዳና በሥሩ በሚገኙ ልዩ ልዩ ቀበሌዎች ውስጥ ስለተመደቡት የምርጫ አስፈጻሚዎችና የሕዝብ ታዛቢዎች ማንነትና ምንነት ከላይ በክፍል አንድ ውስጥ ተገልጾአል:: አሁንም ከዚሁ ወረዳ በተገኘው መረጃ መሠረት:

በአብዛኞቹ የወረዳው ምርጫ ጣቢያዎች ድምጽ መስጠቱ ከቀኑ በ10 ሰዓት ላይ አብቅቷል:: የተቃዋሚዎች የምርጫ ታዛቢዎች በመተማመኛው ሠነድ ላይ እንዲፈርሙ ተጠይቀው ነበር:: ነገር

ግን ቆጠራው ሳይካሄድና ሳይጠናቀቅ አንፈርምም በማለታቸው ተደብድበው ተባረዋል:: በመሆኑም ቆጠራው እነዚህ ታዛቢዎች በሌሉበት ተከናውኗል::

### 3) <u>አሮሬሳ ምርጫ ክልል</u> (ሲዳማ ዞን)

ይህ የምርጫ ክልል የደ/ብ/ብ/ሕ/ክልል ርዕሰ መስተዳድር የሆኑት አቶ ሽፈራው ሽጉጤ ለክልል ምክር ቤት የተወዳደሩበት ነው:: በዚህ የምርጫ ክልል ከላይ በተራ ቁጥር ሐ በተገለጸው ዓይነት ተሰርቀው ከወጡ (ለገዢው ፓርቲ ተላልፈው ከተሰጡ) እና ለታማኝ አባላቱ በቅድሚያ ከታደሉ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች መካከል ጥቂቱ በግንቦት 8 ቀን 2002 ዓ.ም. በእጃቸው ሊገቡ መቻላቸውን የሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን) አመራሮች ገልጸዋል:: ለሲዳማ ዞንና ለሀዋሳ ምርጫ አስፈጻሚ ጽ/ቤቶች (በግልባጭም ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ) በግንቦት 10 2002 ዓ.ም. የክስ ደብዳቤ አስገብተዋል:: ስለ ጉዳዩ በጀርመን ድምጽ ሬድዮም መግለጫ ሰጥተውበታል:: የተያዘውም የድምጽ መስጫ ወረቀት በእጃቸው ይገኛል::

### 4) <u>ሸበዲኖ ወረዳ ለኩ ምርጫ ክልል</u> (ሲዳማ ዞን)

- ከታየዘው ፕሮግራም ውጭ ከንጋቱ 12 ሰዓት በፊት የተቃዋሚ ታዛቢዎች ሣይደርሱ / በሌሉበት ድምጽ መስጠት እንዲጀመር ተደርጓል፤
- በዚህ የምርጫ ክልል በስንታሮ ምርጫ ጣቢያ - 4 በለጠ ዲዳሞ የተባለ መራጭ በሕገ ወጥ መንገድ ያገኛቸውን ሁለት ተጨማሪ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ከራሱ ጋር በአንድ ላይ አራት ወረቀቶች (ሁለት ለዋናው ፓርላማ ሁለት ደግሞ ለክልል ምክር ቤት ድምጽ መስጫዎች) አራቱንም አንድ ላይ አጣጥፎ በድምጽ መስጫ ኮሮጆ ውስጥ ለመክተት ሲታገል በሲአን ተወዳዳሪዎች ተወካይ አማካኝነት እጅ ከፍንጅ ተይዟል:: የምርጫ አስፈጻሚዎቹ ሰውየውን ሕግ ፊት ለማቅረብ ሊተባበሩ ስላልፈቀዱ ድምጽ መስጫ ጣቢያውን ያለችግር ለቆ ሔዷል:: የተያዘው ሕገ ወጥ የድምጽ መስጫ ወረቀት በማስረጃነት በድርጅቱ አመራሮች እጅ ይገኛል::
- በዕለቱ ድምጽ የሰጠው መራጭ ቁጥር ከተመዘገበው መራጭ ቁጥር በላይ ሆኖ ተገኝቶአል::
- በየምርጫ ጣቢያው የቀበሌ ሊቀመንበሮች የገዢው ፓርቲ ወኪል / ታዛቢ ሆነው ተገኝተዋል::

### 5) <u>ወንዶ ገነት ምርጫ ክልል</u> (ኦሮሚያ ዞን)

በወንዶ ምርጫ ክልል የሚኖሩ ገለልተኛ ዜጎችና ተቃዋሚዎች እንደሚሉት ከሆነ፡

- የምርጫ ኮሮጆዎች በሌሊት ይሞሉ ነበር
- የሕዝብ ታዛቢ የተባሉት ሰዎች ሳይቀሩ በድምጽ መስጫ ጣቢያ ውስጥ መራጮች በንብ (ገዢ ፓርቲ) ላይ ምልክት እንዲያደርጉ ሲያግባቡና ሲያስፈራሩ ነበር፤
- የገዢው ፓርቲ ካድሬዎች ከምርጫ ጣቢያ በ30 ሜትር ርቀት ላይ ሆነው (ከምርጫው ሕግ ውጭ) መራጩን ሕዝብ ኢሕአዴግን እንዲመርጥ ሲያዋክቡ ነበር፤
- የተቃዋሚ ታዛቢዎች እንዳይገኙ ማስፈራራት፤ ማሰርና በጥቅም መደለል፤ አንድ በምርጫው ዋዜማ ምሽት በገዢው ፓርቲ አባላት ገንዘብ የተሰጠው የተቃዋሚዎች ታዛቢ፤ በምርጫው ቀን በጊዜ ሊቀሰቅሱት እቤቱ ለተገኙት የተቃዋሚ አባላት እባካችሁ ልኑርበት፤ ልጆቼን ላሳድግበት እናንተን እግዚአብሔር ይርዳችሁ እኔን ግን ተዉኝ ብሎ እንደመለሳቸው ገልጸዋል፤
- በየምርጫ ጣቢያው በአካባቢው ሕዝብ ዘንድ ፈጽሞ የማይታወቁ ሰዎች ድምጽ ሲሰጡ ታይተዋል::

### 6) <u>ጥቁር ውኃ ምርጫ ክልል</u> (ኦሮሚያ ዞን)

- በጥቁር ውኃ ምርጫ ክልል ቁጥር 1 ምርጫ ጣቢያ (ጥቁር ውኃ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት) አንድ የገዢው ፓርቲ ካድሬ በድምጽ መስጫው ሥፍራ ላይ ተቀምጦ መራጮች ለየትኛው ፓርቲ ድምጽ እንደሰጡ ይቆጣጠር ነበር::
- ዕርዳታ የሚያስፈልጋቸው አቅመ ደካማ መራጮች የራሳቸውን ረዳቶች ይዘው እንዲመጡ ሕጉ ቢያዝም ከሕጉ በተጻራሪ ካድሬዎች አብረው እየገቡ በማሳሳት ለገዢው ፓርቲ ድምጽ እንዲሰጡ ያደርጉ ነበር፤
- ይኸው ሕገወጥ አሠራር በምርጫ ጣቢያ ቁጥር 2ም (ፖሊስ ጣቢያ አካባቢ) ሲፈጸም ታይቷል::

## 7) ሐገረ ማርያም ምርጫ ክልል (ኦሮሚያ ዞን)

ከሐገረ ማርያም እንደተገኘው መረጃ ከሆነ:

ሀ) በተርጫ ምርጫ ጣቢያ የተቃዋሚ ዕጩዎች ተደብድበዋል፤ ታዛቢዎቻቸውም ተባረዋል::

ለ) ቁጥራቸው 56 የሚሆን የተቃዋሚዎች የምርጫ ታዛቢዎች በተመደቡበት ምርጫ ጣቢያ እንዳይገቡ ተከልክለው ተመልሰዋል:: ስለዚህ በነዚህ የምርጫ ጣቢያዎች የድምጽ አሰጣጡም ሆነ ቆጠራው የኢሕአዴግ ታዛቢዎች ብቻ በተገኙበት ተፈጽሟል::

ሐ) የተቃዋሚ ተንቀሳቃሽ ታዛቢ የነበረ አቶ አየለ ጋኒ የተባለ ሰው ከዓርብ ግንቦት 13 / 2002 ጀምሮ ይህ ጥንቅር እስከተዘጋጀበት ጊዜ ድረስ በቀርጫ ወረዳ ፖሊስ ጣቢያ ታስሮ ይገኛል::

መ) በምርጫው ቀን ዋዜማ ከሌሊቱ 8 ሰዓት የአካባቢው ካድሬዎች "የሐገር ሽማግሌዎች" የሚባሉ ሰዎችን በማስነሳትና በማስተባበር ለማጭበርበር ቅድመ ዝግጅታቸውን ጨርሰውና ተፈራርመው ነው ያደሩት፤ መራጮችም ጠዋት ሲገቡ የጠበቃቸው ቀድሞ የተሠራ ነገር ነው::

ሠ) የሌሊቱ አልበቃ ብሎ የገዥው ፓርቲ/መንግሥት የአካባቢው ኃላፊዎች፤ ከፍተኛ ካድሬዎችና አባላት በየምርጫ ጣቢያው በአካል በመገኘትና በድምጽ መስጫ ሥፍራዎች ሳይቀር በመግባት መራጮችን እያስፈራሩ በገዢው ፓርቲ የምርጫ ምልክት (ንብ) ላይ ምልክት በማድረግ እንዲመርጡ በግልጽ ሲያስገድዱ መዋላቸውን የተመለከቱ የዓይን ምስክሮች አረጋግጠዋል::

(ይህ በሐገረ ማርያም ተረጋግጧል የተባለው የገዢው ፓርቲ ሰዎች የሌሊት ሥራ በአንዳንድ የደቡብ ክልል ከተሞችም በተመሣሣይ መልኩ መፈጸሙን የሚጠቁሙ ያልተለመዱ የሌሊት የጥድፊያ እንቅስቃሴዎች፤ የብዙ ወንዶችና ሴቶች የሹክሹክታ ድምጾችና የእግር ኮቴ ድምጾች፤ በር ቁርቆራዎችና የመሳሰሉ ሁኔታዎች እንደነበሩ አዳምጠናል ያሉ ጥቂት ዜጎችም አጋጥመዋል:: ተሰርቀው የወጡ (ለገዢው ፓርቲ ተላልፈው የተሰጡ) እና ለታማኝ አባላቱ በቅድሚያ ታደሉ የተባሉት የድምጽ መስጫ ወረቀቶች በኮሮጆ ውስጥ የተጨመሩት ከሌሊቱ 8 እስከ 9 ሰዓት በነበረው ጊዜ ነው የሚል ያልተረጋጠ ስሞታም ተሰምቷል:: ይህም ሊጣራ ይገባዋል)::

ሌላም የምርጫ ማጭበርበር ድርጊት መረጃ ተገኝቶአል:: ይኸውም በድምጽ መስጫው ቀን በህመም፤ በወሊድ፤ በሥራና በሌሎችም ልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሳ ያልተገኙ ነገር ግን የተመዘገቡ መራጮች ማንነት ከመዝገብ እየታየ በስማቸው ለገዢው ፓርቲ ድምጽ መሰጠቱ ነው:: ይህ መረጃ የተገኘው በአንድ የምርጫ ጣቢያ ውስጥ በጸጥታ ጥበቃና በፍተሻ ሥራ ተመድቦ ቀኑን ሙሉ እዚያው ከዋለና በአይኔ አይቻለሁ ካለ የገዢው ፓርቲ የወጣት ሊግ አባል ነው:: ይህ ምናልባት በሁሉም አካባቢዎች በተመሣሣይ ተፈጽሞ ይሆናል የሚል ጥርጣሬ ያሳድራል::

ረ) በመልካ ሶዳ ምርጫ ክልል የሚከተሉት የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት በሕጋዊ የምርጫ ቅስቀሳ ላይ እያሉ ተይዘው ፍንጬዋ ፍርድ ቤት ቀርበው በከፍተኛ ፍጥነት እያንዳንዳቸው የሁለት ዓመት እስራት ተፈርዶባቸው አሁን በባሌ ማረሚያ ቤት ታስረው ይገኛሉ:

1) አቶ ጋዩ ዳንቢ
2) አቶ ጌዶ ሹቁሌ
3) አቶ ቡሌ ቦላ

## ማጠቃለያ

ዝርዝር መረጃዎችን ለጊዜው ማግኘትና ማረጋገጥ ባይቻልም በአጠቃላይ በወላይታ፤ በአርባምንጭ፤ በኮንሦ፤ በዲላ፤ በይርጋጨፌ፤ በሞያሌም በአጠቃላይ የምርጫው ሒደት ላይ ተመሣሣይ ሕገ ወጥ ተግባሮች ሲፈጸሙ እንደነበር ሐገር ወዳድ ዜጎች በስልክ ገልጸዋል::